አሀዛዊ መረጃ

ICRC

ኢትዮጵያ

# አሀዛዊ መረጃ

## ከጥር እስከ ታህሳስ 2021 (እአአ)



ICRC

የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ (ዓአቀመኮ) ተግባሩን በኢትዮጵያ የጀመረው እአአ በ1977 ዓ.ም በኢትዮጵያ እና ሱማሌ መካከል ከተካሄደው የትጥቅ ግጭት አንስቶ ነው። የዓአቀመኮ በአሁኑ ጊዜ የሚያከናውነው ዋና ተግባር በአገሪቱ በትጥቅ ግጭት እና በሌሎች ብጥብጦች ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች እርዳታ መስጠት ነው። እአአ በ2021 ዓ.ም የዓአቀመኮ የሰብዓዊነት እንቅስቃሴዎች በዋናነት ያተኮሩት በሰሜን ኢትዮጵያ በተከሰተው ውጊያ ምክንያት ለተፈጠረው የሰብዓዊነት ቀውስ ምላሽ በመስጠት እና በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች በጎሳ ግጭት ሳቢያ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች እርዳታ በማቅረብ ላይ ነው። የዓአቀመኮ በ2021 ዓ.ም (እአአ)፧

### ጤና

- በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ 44 የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ጣቢያዎች እና 57 ሆስፒታሎች የአስቸኳይ ጊዜ አቅማቸውን እና የኮቪድ በሽታን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር እንዲችሉ መሠረታዊ የጤና መገልገያዎችን፣ በአስቸኳይ ጊዜ የቆሰሉ ሰዎችን ለማከም የሚያስችሉ ቁሳቁሶችን የያዙ ሣጥኖችና የግል ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ሰጥቷል። አቅርቦቶቹ 4,250 በጽኑ የቆሰሉ ወይም 13,450 በመለስተኛ ደረጃ የቆሰሉ ሰዎችን እና 116,100 ሌሎች ታካሚዎችን ለማከም ይረዳሉ። ከዚህ በተጨማሪም የዓአቀመኮ በጤና ሚኒስቴር ሥር ላሉ የጤና ተቋማት የሚሰራጩ ዊል ቼሮችን እና የአካል ድጋፎችን የመሳሰሉ የመንቀሻቀሻ መሣሪያዎችን ለሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ ሰጥቷል።
- የስሁል ሽሬ ሆስፒታል በአስቸኳይ ጊዜ የሚጠቀምበት የኦክስጂን (በየወሩ 75 ሲሊንደሮች) ድጋፍ አድርጓል። እንዲሁም የዓአቀመኮ በኦሮሚያ ለሚገኙ 4 ሆስፒታሎች እና በሁመራ ለሚገኝ 1 ሆስፒታል የኮቪድ በሽታን እና ሌሎች የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎችን በአግባቡ ለመያዝና የኦክሲጅን መጓጓዣ ወጪን ለመሸፈን እንዲችሉ የገንዘብ ድጋፍ አደርጓል።
- በኦሮሚያ ክልል ለሚገኘው ደምቢ ዶሎ አጠቃላይ ሆስፒታል እና በትግራይ ክልል ላለው የስሁል ሽሬ አጠቃላይ ሆስፒታል የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ አቅማቸውን ለማጎልበት የሚያስችል የቴክኒክ ድጋፍ ሰጥቷል።
- በኦሮሚያና በሱማሌ ክልል ውስጥ ለሁሴ፣ ጭናቅሰን፣ ቱሊጉሌድ፣ መዩ፣ ኢናንጎ እና ጉሊሶ ወረዳዎች ለሚገኙ 6 የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ጣቢያዎች ወርሀዊ የቴክኒክ እገዛ፣ የህክምናና የድህረ-ወሊድ መገልገያዎች እና የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች አቅርቧል። እንዲሁም የዓአቀመኮ በትግራይ ክልል ለሚገኙ 11 የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ጣቢያዎች ተመሳሳይ ድጋፍ አድርጓል። እነዚህ አቅርቦቶች በጤና ጣቢያዎቹ ልጆቻቸውን ለተገላገሉና ቁጥራቸው ከ5,350 በላይ የሆኑ እናቶችን ተጠቃሚ አድርጓል።




የዓአቀመኮ በአማራ ክልል ለሚገኘው ፍኖተ ሰላም አጠቃላይ ሆስፒታል የሀክምና መገልገያ መሳሪያዎችን ሲሰጥ (አአአ 2021 ዓ.ም)

- በአማራ፣ ትግራይ፣ ኦሮሚያ፣ ሀረር፣ ሱማሌ፣ በድሬ ዳዋ እና አዲስ አበባ ክልሎች ለሚገኙ 15 የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር (ኢቀመማ) 1,800 የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ሳጥኖችን በህክምና ቁሶች መልሶ ለመሙላት የሚያሰችል እገዛ አድርጓል።
- በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ወለጋ ከሚገኙ 10 የጤና ተቋማት ለተውጣጡ 15 የጤና ባለሙያዎች በመሠረታዊ የድንገተኛ ወሊድ እና አዲስ በተወለዱ ህፃናት እንክብካቤ ላይ ያተኮረ የ12 ቀናት ስልጠና አዘጋጅቷል።
- ከደምቢዶሎ አጠቃላይ ሆስፒታል ለተውጣጡ 12 የጤና ባለሙያዎች የስሜት መረበሽን (Emergency trauma) በአግባቡ ለመያዝ የሚያስችል የመጀመሪያ ደረጃ ስልጠና ሰጥቷል።
- ከሱማሌ፣ ኦሮሚያና ድሬዳዋ ክልሎች ውስጥ ከሚገኙ 8 የጤና ተቋማት ለተውጣጡ 48 የጤና ባለሙያዎች በበሽታ መከላከልና መቆጣጠር ላይ ያተኮረ ስልጠና አዘጋጅቷል።
- ከአዲስ አበባ እና አዲግራት ቅርንጫፎች ለመጡ 42 የኢቀመማ የአምቡላንስ ረዳቶች እና የጤና ባለሙያዎች የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና አሰጣጥ ስልጠና ሰጥቷል።
- በትግራይ ክልል ውስጥ በፆታ ጥቃት ጉዳት ለደረሰባቸው በስድስት ማቆያ ማዕከሎች ለሚገኙ ሴቶች የመሰረታዊና ክብር መጠበቂያ ቁሳቁሶች ድጋፍ አድርጓል።

## የኢኮኖሚ ዋስትና

- በትግራይ ክልል በተከሰተው ውጊያ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው 16,139 በግብርና የሚተዳደሩ አባወራዎች የጤፍ እና የማሽላ ዘር እህል እንዲሁም የማዳበሪያ እርዳታ በማድረግ 96,834 የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ አድርጓል።
- በኦሮሚያ ክልል በጭናቅሰን፣ ባቢሌ እና ሀሮሊሙ ወረዳዎች ውስጥ በጎሳ ግጭት ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው 10,000 አባወራዎች (60,000 ግለሰቦች) የበቆሎ እና ማሽላ ወይም የአኩሪ አተር ወይም የስንዴ እና ማሽላ ዘር እህል እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።
- በሱማሌ ክልል በቱሊጉሌድ ወረዳ በጎሳ ግጭት ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የስንዴ እና ማሽላ ወይም የበቆሎ እና የማሽላ ዘር እህል በመስጠት 5,000 አባወራዎችን (30,000 የቤተሰብ አባላትን) ተጠቃሚ አድርጓል።
- በአማራ፣ አፋር፣ ኦሮሚያ፣ ሱማሌ እና ትግራይ ክልሎች ውስጥ ባሉ የተለያዩ መጠለያዎች ተጠልለው ለሚገኙ 61,628 ተፈናቃይ አባወራዎች (396,972 ግለሰቦች) መሰረታዊ የቤት ቁሳቁሶችን አከፋፍሏል።




በደሴ ከተማ አማራ ክልል ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች የዓአቀመኮ እና ኢቀመማ በጋራ ያሰራጯቸውን መሠረታዊ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ሲውስዱ (አአአ 2021 ዓ.ም)

- ከሐራማያ ዩኒቨርሲቲ በተገኘ የቴክኒክ ድጋፍ በጭናቅሰን ወረዳ ሊሚገኙ 9 የኅብረት ሥራ ማኅበራት የዘር እህል ለማባዛት እንዲችሉ መሠረታዊ የዘር እህልና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ  በጎሳ ግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው 180 አርሶ አደሮች የዘር እህል እንዲያገኙ አድርጓል።
- ከሱማሌ ምርጥ ዘር ድርጅት በተደረገ የቴክኒክ ድጋፍ አማካኝነት በቱሊጉሌድ ወረዳ ለሚገኙ 11 የኅብረት ሥራ ማኅበራት የዘር እህልና የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል። ይህ ድጋፍ በጎሳ ግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው 220 አርሶ አደሮች የዘር እህል እንዲያገኙ አስችሏል።
- በሱማሌና ኦሮሚያ ክልሎች የሚገኙ 685,783 የቤት እንስሳዎች የጸረ ከብት በሽታ ክትባት በመስጠት 44,300 አርብቶ አደር ቤተሰቦችን (265,800 ግለሰቦችን) ተጠቃሚ አድርጓል።

- የ1,460 አርብቶ አደር ቤተሰብ ንብረት ለሆኑ 2,119 የቤት እንስሳት በመረጃ ላይ የተመሠረተ የእንስሳት እርባታ መድህን ወጪን 70 በመቶውን የሸፈነ ሲሆን ይህም 2,760 ግለሰቦችን ተጠቃሚ አድርጓል።
- ለ43,150 አባዎራዎች (258,900 ግለሰቦች) መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ሊያሟላ የሚችል ሁለገብ የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል።
- በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ለሚገኙ ተፈናቃዮች መሰረታዊ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን የያዙ 8,034 ሳጥኖች እና 5,500 በፀሐይ ኃይል የሚሰሩ ባትሪዎችን ለኢቀመማ ለግሷል።
- በትግራይ ክልል የሚገኙ የጤና ተቋማት በደመወዝ መቋረጥ ምክንያት የጤና አገልግሎት እንዳይቋርጥ ለማድረግ በ18 የጤና ተቋማት ለሚሰሩ ሰራኞችና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ለተቋሞቹ ታካሚዎቸ 237,225 ኪግ ስንዴ፣ 23,760 ኪግ ሽምብራ፣ 7,130 ሊትር ዘይት እና 3,186 ኪግ ጨው ለግሷል።

## ውሀና የመኖሪያ አካባቢ

- በመቀሌ፣ አድዋ፣ አክሱም፣ ሽሬ፣ አዲግራት እንዲሁም በማይጸብሪ እና ህጻጼ አካባቢዎች ባሉ የተፈናቃዮች መጠለያ ካምፖ`ች ውስጥ ለሚገኙ የውሀ ማሰራጫ ጣቢያዎች የውሀ ማጣሪያ ኬሚካሎችን ከመለገሱም በተጨማሪ ለተፈናቀዮቹና ለነዋሪዎቹ ውሀ በቦቴ የማቅረብ አገልግሎት ሰጥቷል። ከዚህም በተጨማሪ የዓአቀመኮ ለዉሀ ማሰራጫ ጣቢያዎቹ ጄኔሬተሮች እና በመሬት ውስጥ የሚቀበሩ ፓምፖ`ችን ለግሷል። ይህም ድጋፍ በተጠቀሱት ቦታዎች የሚኖሩና ቁጥራቸው ከ1.74 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎችን የመጠጥ ውሀ አግልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችሏል።
- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር በመቀሌ፣ አዲግራት፣ አክሱም፣ አድዋ እና ሽሬ ከተሞች በሚገኙ መጠለያዎች ለተጠለሉ 78,018 ተፈናቆዮች በንፅህና አጠባበቅ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን ሰጥቷል።




በአማራ ክልል ጋንጋ አካባቢ በሰሜን ኢትዮጵያ በተካሄደው ጦርነት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች የዓአቀመኮ እድሳት ካደረገለት የውኃ ጣቢያ ውሀ ሲቀዱ (ኦኦኦ 2021 ዓ.ም)

- በሽሬ ስሁል ሆስፒታል፣ ሽሬ፣ መቀሌና በሁመራ ሆስፒታሎች እንዲሁም በመቀሌ የአካል ጉዳተኞች ማቋቋሚያ ማዕከል ውስጥ የሚገኙ 5 የጤና ተቋማትን የውሀና የጽዳት አገልግሎት አውታሮችን በማደስ 363 ታካሚዎችን የተሻሻለ የውሀና የጽዳት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል።
- በአማራ ክልል በንፋስ መውጫ፣ጋሳይ እና ደብረዘቢጥ ከተሞች ለሚገኙ የውሀ ማሰራጫ ጣቢያዎች የኤሌክትሮ መካኒካል መሣሪያዎችን በመስጠት በጦርነት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው አገልግሎቶች መልሰው አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ የዓአቀመኮ ለደብረ ብርሀን ሆስፒታል አንድ ጄኔሬተር በመለገስ 64,644 ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።
- በሱማሌ ክልል አውጃቡር፣ ቡርቃ፣ ጋቦጋቦ፣ ቱሉጉሌድ ከተሞች እንዲሁም በጉርሱም እና ኦዳሳናትሌ አካባቢዎች 6 የገጠር የውሀ አቅርቦት ፕሮጀክቶችን አጠናቅቆ 37,608 ሰዎችን ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል።
- በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ጉጂ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ እና ኢሉ አባቦራ ዞኖች ውስጥ የሚገኙ የእጅ ፓንፖ`ችን በማደስና እና ለደምቢ ዶሎ ከተማ የውሀ ማጣሪያ ኬሚካሎችን በመለገስ 31,428 ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።
- በየቀኑ 183 ታካሚዎችን ተጠቃሚ ያደረገውን በነገሌ፣ ሀዋ ገላን እና ደምቢ ዶሎ ሆስፒታሎች እና በጉሊሶ የጤና ጣቢያ የሚገኙ 4 የውሀና ጽዳት አገልግሎቶችን አድሷል።
- በኢንድሪስ፣ ዘራቢት፣ አዲህርዲ፣ ኮራሪት፣ ዲቪዥን እና ሌሎች አካባቢዎች በእጅ የሚሠሩ 80 የውኃ ፓምፖ`ችን በማደስ በትግራይ ክልል በተከሰተው ጦርነት ምክንያት ችግር የገጠማቸው 104,225 ሰዎችን የውሀ አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪም የጄኔሬተር ባትሪዎችን እና 135 ጀሪካን በረኪና ለሁመራ ሆስፒታል በመለገስ በውጊያ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች የተሻሻለ የጤና አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ አድርጓል።
- ለማይካድራ፣ዳንሻ እና ሁመራ ጤና ተቋማት 3 የጄኔሬተር ባትሪዎችን በመለገስ 330 ታካሚዎች በየዕለቱ የጤና አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ አድርጓል።

## ማረሚያ ቤቶች

- በመላው አገሪቱ በሚገኙ 42 ማረሚያ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ 31,069 ታራሚዎችን የጎበኘ ሲሆን 796 ታራሚዎችን በግለሰብ ደረጃ ተከታትሏል።
- በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ 33 ማረሚያ ቤቶች የመዝናኛ መገልገያዎችን ጨምሮ የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች፣ አልባሳትና የብርድ ልብሶች ድጋፍ በማድረግ 25,794 ታራሚዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።
- ለ763 ታራሚዎች ነጻ የስልክ ጥሪ እና የአየር ሰዓት አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማስጀመር/ለማስቀጠል አስችሏል።
- ከተለያዩ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ለተውጣጡ 21 የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ሠራተኞች በማረሚያ ቤት አስተዳደር ዙሪያ ያተኮረ ስልጠና እንዲሁም በማንዴላ ህጎች ላይ ያተኮረ ሌላ ስልጠና ለ54 ወታደራዊ ፖሊሶች አዘጋጅቷል።
- በጊምቢ ማረሚያ ቤት (ኦሮሚያ ክልል) 1,866 ታራሚዎችን ተጠቃሚ ያደረገ የውሀና ጽዳት አገልግሎት ግንባታን አጠናቋል።
- የ21 ፕሮጀክቶች ግንባታ፣ጥገና እና እድሳት ስራዎችን በማጠናቀቅ በ37 ማረሚያ ቤቶች የሚገኙ 24,130 ታራሚዎች የተሻሻለ የውሀ፣ የጽዳትና የኃይል አቅርቦት አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጓል ።
- ለቃሊቲ ፌደራል ማረሚያ ቤት ክሊኒክ እና የታካሚ መቀበያ ክፍል የመንቀሳቀሻ መሣሪያዎች (የክራንች፣ ስትሬቸሮች እና ዊልቼር) በመለገስ 2,100 ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ ታራሚዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።
- በማረሚያ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያተኮረ የ4 ቀናት ሴሚናር ከ6 የክልልና ፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽኖች ለተውጣጡ 21 ከፍተኛ የማረሚያ ቤት ጤናና ደኅንነት ሠራተኞች አዘጋጅቷል።
- ከኦሮሚያ፣ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ሀረሪ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ እና ሱማሌ፣ ከአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ክልሎች ለተውጣጡ 18 የክልል እና የፌደራል ጤና ጥበቃ አስተባባሪዎች እና የደህንነት ሠራተኞች በማረሚያ ቤት ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያተኮረ የ2 ቀን ሴሚናር አዘጋጅቷል።
- በዳለቲ፣ ደብረ ብርሀን፣ ጎንደር፣ ከሚሴ እና ያቤሎ በሚገኙ ማረሚያ ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ 65 የአዕምሮ ህሙማን፣ ነፍሰ ጡር ሴቶች እና ልጆቻቸው ክብራቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸው የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን እና አልባሳትን ሰጥቷል።
- ለዳለቲ፣ ጎንደር፣ ከሚሴ፣ መቀሌ እና ያቤሎ ማረሚያ ቤቶች 20,000 ያህል ታራሚዎችን ተጠቃሚ ያደረገ የህክምና እና ህክምና ነክ ያልሆኑ መገልገያዎችን ለግሷል። በተጨማሪም የዓአቀመኮ የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ አቅማቸውን ለማጠናከር እንዲረዳ ለደብረ ብርሀን፣ ይርጋለም፣ ዳሊቲ እና መቀሌ ማረሚያ ቤቶች የህክምና እና ህክምና ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን በመስጠት 22,000 ያህል ታራሚዎች የተሻሻለ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጓል።
- ለሀዋሳ እና አሶሳ ማረሚያ ቤቶች የግል ብክለት መከላከያ መሣሪያዎችን የሰጠ ሲሆን የኮሮና ቫይረስን ጨምሮ ሌሎች ተላላፊ በሽታዎችን ስርጭት ለመቆጣጠር ይረዳ ዘንድ ለቀዳማይ ወያኔ እና ቃፍታ ሁመራ ፖሊስ ጣብያዎች እንዲሁም ለያቤሎ እና ይርጋለም ማረሚያ ቤቶች በሽታን ለመከላከል የሚረዱ መሣሪያዎችን አቅርቧል። አቅርቦቶቹ ወደ 7,800 የሚጠጉ ታራሚዎችን ተጠቃሚ አድርገዋል።

## የተነጣጠሉ ቤተሰቦች

- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ የለይቶ ማቆያ ማዕከሎች ውስጥ ለነበሩና ከስደት ለተመለሱ 112,992 ኢትዮጵያዊያን የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች እርዳታ አድርጓል።




ከቤተሰቧ የተነጠለች አንዲት ሴት በዓአቀመኮ እገዛ ለቤተሰቦቿ ስልክ እየደወለች፤ ሽሬ፤ትግራይ ክልል (አአአ 2021 ዓ.ም)

- 46,372 ከስደት ተመላሾች ኢትዮጵያ ሲደርሱ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ግንኙነት ለማድረግ እንዲችሉ የስልክ ጥሪ አገልግሎት አቅርቦት አድርጓል።
- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር ለስደተኞች እና በትግራይ ውስጥ የመገናኛ ዘዴ ባለመኖሩ ምክንያት ሌሎች ከሚወዷቸው ሰዎች ጋር መገናኘት ላልቻሉ ሰዎች 115,745 ነጻ የስልክ ጥሪዎችን በማቅረብ የቤተሰብ መልዕክት እንዲለዋወጡ አድርጓል።
- በኢትዮጵያ እና በውጭ አገራት የጠፉባቸው ዘመዶቻቸውን በመፈለግ ላይ ካሉ ሰዎች 2,794 የአፋልጉኝ ጥያቄ የተቀበለ ሲሆን ከነዚህም መካከል የ107 ተፈላጊ ሰዎችን አድራሻ አግኝቷል።

- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር በግጭት ወይም በብጥብጥ ምክንያት የተነጣጠሉ የቤተሰብ አባላት የቃል መልእክቶችን ጨምሮ 17,430 የቀይ መስቀል መልዕክቶችን እንዲለዋወጡ አድርጓል።

## የአካል ጉዳተኞች

- ወደ 9,900 የሚጠጉ አካል ጉዳተኞች የዓአቀመኮ እርዳታ በሚያደርግላቸው 11 የአካል ጉዳተኛ ማቋቋሚያ ማዕከሎች ውስጥ የአካል ጉዳተኛ አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጓል።
- ለ57 ታራሚዎች አጠቃላይ የአካል ጉደተኛ ማቋቋሚያ ድጋፍ (የአካል ድጋፍ መሣሪያዎች፣ ዊልቼር፣ ክራንች፣ ምትክ ጫማ፣ የሰው ሰራሽና አካል ድጋፍ) አድርጓል።




የመቀሌ የአካል ጉዳተኞች ማቋቋሚያ ማዕከል ሠራተኞች በሰው ሰራሽና አካል ድጋፍ ምርት ላይ ስልጠና ሰወስዱ መቀሌ፣ ትግራይ ክልል (አአአ 2021 ዓ.ም)

- በማረሚያ ቤት ላሉ 8 የፊዚዮቴራፒስቶች እና የአካል ጉዳተኞች ማቋቋሚያ አገልግሎት ሠራተኞች የአንድ ቀን ገለጻ ሰጥቷል።
- ለ13 የፊዚዮቴራፒ ባለሙያዎች፣ ነርሶች እና የሰው ሰራሽና አካል ድጋፍ ባለሙያዎች በስኳር ህሙማን የእግር እንክብካቤ አያያዝ ላይ ያተኮረ የአንድ ሳምንት ስልጠና ሰጥቷል።

## መከላከል

- በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ መሠረታዊ መስፈርቶች ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች ለ253 የኢትዮጵያ መከላከያ ሀይል መኮንኖች ሰጥቷል።
- ለ150 የኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ሠራዊት ልዩ ኦፕሬሽን አባላት በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ መሠረታዊ መስፈርቶች ላይ ያተኮረ ስልጠና አዘጋጅቷል።
- ለ50 የአማራ ክልል ሚሊሻ አባላት በዓለም አቀፍ ሰብዓዊነት እና ሰብዓዊ መብቶች ህግ እና መስፈርቶች ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን ሰጥቷል።
- ከተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ሠራዊት ለተውጣጡ 50 የጦር መኮንኖች በባህር እና በሳይበር ጦርነት ላይ ተፈጻሚ በሚሆኑ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ ደንቦች ላይ ያተኮረ ስልጠና ሰጥቷል።




የፌዴራል እና የኦሮሚያ ፖሊስ አባላት በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ እና የሰብአዊ መብት መስፈርቶች ባተኮረ ሴሚናር ላይ ሲሰተፉ፤ ሻምቡ፣ ሆሮጉዱሩ፤ ወለጋ ዞን፤ ኦሮሚያ ክልል (አአአ 2021 ዓ.ም)

- በባህር ዳር ከተማ ለ53 ወታደራዊ ፖሊሶች በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ መሠረታዊ መስፈርቶች ላይ ያተኮረ ሴሚናር አዘጋጅቷል።
- ከኢትዮጵያ ጦር ኮሌጅ ጋር በኮሌጁ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግን ለማካተት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ፈርሟል።
- ለ273 የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን አባላት እና የሶማሌ፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የሲዳማ፣ የሀረሪና የድሬዳዋ ክልሎች መደበኛ እና ልዩ ኃይል እንዲሁም የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን አባላት በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት መስፈርቶች ላይ (ከሀይል አጠቃቀም ጋር በተገናኘ መልኩ) ስልጠና ሰጥቷል።
- ከኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ፖሊስ በምርጫ ወቅት ስላለው ስልጣን እንዲሁም በሰብዓዊነት መስፈርቶች ላይ ያተኮረ የአሰልጣኞች ስልጠና ለ79 ፌዴራልና ክልል ፖሊስ መኮንኖች ሰጥቷል። በተጨማሪም የዓአቀመኮ ከዚሁ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ሰብዓዊ መብቶች በዩኒቨርሲቲው ሥርዓተ ትምህርት እና ሞዱዩልስ ውስጥ ለማካተት የሚረዳ የአሰልጣኞች ስልጠና ሰጥቷል.።
- በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግና ሰብዓዊ መብት መስፈርቶችና በአጀብ አያያዝ ላይ ያተኮረ አውደ ጥናት ለ40 ሱፐርባይዘር ፖሊስ መኮንኖች አዘጋጅቷል።

- በባህር ዳር ከተማ ለ35 ጋዜጠኞች በሰብዓዊነት ዘገባ ላይ ያተኮረ ስልጠና ሰጥቷል፡፡
- ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በግጭት ወይም በሌሎች ብጥብጦች ወቅት ለጤና አገልግሎት ከለላ በመስጠት ላይ ያተኮረ ሴሚናር ለ15 ዩኒቨርሲቲ መምህራን፣የጤና ባለሙያዎችና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አዘጋጅቷል፡፡
- ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር 19 ዩኒቨርሲቲዎች የተካፈሉበትን 5ኛውን የዓለም አቀፍ ህግ ምስለ ችሎት ውድድር አዘጋጅቷል፡፡
- በአሩሻ ታንዛኒያ በተካሄደው የመላው አፍሪካ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ ምስለ ችሎት ውድድር ላይ የተሳተፉትን 2 ተማሪዎችን ስፖንሰር አድርጓል፡፡

## ከኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኀበር ጋር የተደረገ ትብብር

- በሰሜን ኢትዮጵያ እና በወለጋ ዞኖች (ኦሮሚያ ክልል) ለ164,240 ቁስለኞች እና ለሌሎች ህሙማን አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ የ43 የአምቡላንሶችን ወጪ ሸፍኗል፡፡
- የ8,000 ቤተሰቦችን (40,000 ግለሰቦችን) ፍላጎት ለመሸፈን የሚችሉ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ለኢቀመማ ለግሷል፡፡
- 22 ቅርንጫፎች የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና አሰጣጥ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን ለማዘጋጀት እንዲችሉ ለኢቀመማ ድጋፍ ያደረገ ከመሆኑም በላይ ለ660 በጎ ፈቃደኛ ሠራተኞች አግባብ ያለው ስልጠና ሰጥቷል፡፡
- ከ6 ክልሎች ለተወጣጡ ለ50 የቀይ መስቀል ሰራተኞች እና በጎ ፈቃደኞች በመጀመሪያ ህክምና አሰጣጥ ላይ ያተኮሩ ሁለት የአሰልጣኞች ስልጠናዎች አዘጋጅቷል፡፡




በኢትዮጵያ የዓአቀመኮ ልዑክ ኃላፊ ኒኮላስ ቮን አርክስ (በስተቀኝ) እና የኢቀመማ ዋና ጸሃፊ ጌታቸው ታአ በሁለቱ ድርጅቶች መካከል ስለሚካሄደው ትብብር አሰመልክቶ የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ሲፈርሙ፤ አዲስ አበባ (አአአ 2021 ዓ.ም)

- 7 የኢቀመማ ቅርንጫፎች ቢሮዎቻቸውን እና መጋዘኖቻቸውን ለማደስ የሚያስችል ድጋፍ አድርገዋል፡፡
- 18 የአምቡላንስ ተሽከርካሪዎችን እና ስድስት ላንድ ክሩዘሮችን ለትግራይ እና ኦሮሚያ ዞን ኢቀመማ ቅርንጫፎች ለግሷል፡፡
- ደህንነቱ በተጠበቀ የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን እና በአደጋ ምላሽ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን ለማዘጋጀት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን አመቻችቷል፡፡
- የወጣቶች ክለቦች ለማቋቋም ለሚረዱ 320 የቀይ መስቀል በጎ ፈቃደኞች 8 ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ረድቷል፡፡

facebook.com/ICRCAfrica
twitter.com/ICRC_Africa
instagram.com/icrc_afrique

**አዲስ አባባ ልዑክ**
**የዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ (የዓአቀመኮ)**
**ቦሌ ክ/ከ, ቀ. 12/13 የቤ ቁ .498**
**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**
**ስ +251 (0)11 647 83 00**

ነቀምቴ ንዑስ ልዑክ
**የዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ (የዓአቀመኮ)**
ካሶ ክ/ከ, ቀ.05, ቀ. 290
ነቀምቴ ኢትዮጵያ
T +251 (0)57 660 66 55

መቀሌ ንዑስ ልዑክ
**የዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ (የዓአቀመኮ)**
ሀደን ክ/ከ, ቀ. 18
መቀሌ ኢትዮጵያ
T +251 (0)34 440 24 40

ሽሬ ንዑስ ልዑክ
**የዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ (የዓአቀመኮ)**
ስ +251(0) 03 42 44 08 73
ቀ.03, ሽሬ ኢትዮጵያ

ጅግጅጋ ንዑስ ልዑክ
**የዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ (የዓአቀመኮ)**
ቀ. 10, የቤ ቁ 196,
ጂግጅጋ ኢትዮጵያ
ስ +251 (0)25 278 81 49

ሽፋን ፎቶ: ዓአቀመኮ
በሰሜን ኢትዮጵያ ባለው ውጊያ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች የመሰረታዊ የቤት ቁሳቁስ እርዳታ ሲወስዱ፡፡

የዓአቀመኮ በዓለም ዙሪያ በትጥቅ ግጭትና በሌሎች ብጥብጦች ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ሰብዓዊ ክብራቸው እንዲጠበቅና የሚደርስባቸውን ስቃይ ለመቀነስ የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡ ይህን የሚያደርገው በአብዛኛው ከቀይ መሰቀልና ቀይ ጨረቃ ማህበራት ጋር በመተባበር ነው፡፡ እንዲሁም ድርጅቱ በግጭት ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን ተፅዕኖ/ስቃይ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግን በማራመድና በማጠናከር እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት መርሆዎችን በደንብ እንዲታወቁ ጥረት ያደርጋል፡፡

ICRC